አቡነ ሙሴ በእንግላንድ የፈጸሙትን በደልና ስህተት አሁንም በጀርመን አገር ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስና ሕዝበ ክርስቲያንን ለመበታተን ከኢትዮጵያ ተነስተው **“ነሐሴ ፳፬እና ፳፭፤፳፻፭ ዓ/ም በግብጾች ገዳም በተካሄደው ስብሰባ ላይ አቡነ ሙሴ በጀርመን መንበረ ጵጵስና አቋቁሜያለሁ” ጥቅምት ፳፻፮፤ ዓ/ም ይድረስ ለአቶ መስፍን አብርሃ/ማኅሌት ሰለሞን ከጀርመን/” የሚል የቀረበ ጽሁፍ በኢትዮሜዲያ ተለጥፎ አይቸ ነው። በሊቀ ካህናት ዶ/ር መራዓዊ ተበጀ ላይ በካድሪዎቻቸው አማካይነት ዘመቻ እንደከፈቱባቸው አየሁ።** አሁንም እኒህ አባት በመሞቻቸው ጊዜ ከስህተታቸው አይማሩም ወይ? የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ለዚህ መከራ የተዳረገችው እሳቸው ለኩሰውት የሄዱት እሳት ነው። እንደገና ከለንደን ውጭ ያሉትን ማህበራት ከፋፈለ እሷንም ጭራሹን እንድትዘጋ አደረገ። የኒህን አባት ምንነት ከማውቀው ትንሽ ልበል፤ አቡነ ሙሴ ከአባ ጳውሎስ ጋር ተጣልተው ወደ እንግሊዝ አገር መጥተው ጥገኝነት ጠይቀው ለአምስት ዓመት ያህል ተቀምጠው ነበር። በኋላ ግን አላማቸው ሳይሳካ ሲቀር በውጭ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያምን ምእመናኑን ከሁለት ከፍለው እሳቸው ዋና ተዋናዋይ ሁነው እርስ በርሱ አፋጅተው ሲያበቁ ጥለው ወጡ። ፺፯ (በ97) ምርጫ በተነሳው ብጥብጥ ከሁለት መቶ በላይ ሰዎች በአደባባይ ሲረሸኑ የክርስትና እምነት አባት እንደመሆናቸው መጠን ለሞቱት ቤተሰቦች ጥናቱን ይስጣችሁ ሳይሉ፣ ደግሞም ለገዛ ወገኖቻቸው ፍትሐት ሳያስፈቱ (በ2004) በሱናሚ ላለቁት ለእስያ ሰዎች የኀዘን ቀንና ፍትሃት ሲያደርጉ በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ በጣም ተሰማው። በዚህ የተነሳ የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ካህናትና ሕዝበ ክርስቲያን በቅዳሴ ስነስርአት የአባ ጳውሎስ ስም እንዳይጠራ በሚል አጸደቀ። አባ ሙሴም “ትንሽ ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ” እንደ አበው አባባል እኒህ መነኩሴም ሃይማኖትን ሳይሆን ሥጋን አስበልጠው ለአባ ጳውሎስ ደጋፊ በመሆን ዘራፍ አሉ። የተወሰኑትን ካህናት መቅደስ ውስጥ ገብታችሁ እንዳትቀድሱ መልሶም መስቀል እንዳታሳልሙ ብለው በስልጣናቸው አወገዙ። በኋላም እሳቸውን ተከትለው ለሄዱት የሥላሴን ቤተ ክርስቲያን ከፍተው አቋቁመው መርቀው ሰጧቸው። በዚህ ምክንያት ለአባ ጳውሎስ አስደስተው የተያዘባቸው ቂም በይቅርታ እንዲዘጋና ወደ ሀገራቸው ተመልሰው አገርቤት ካለው ሲኖደስ ጋር እንዲቀላቀሉ ተደረገ። በመቀጠልም የሰሜን አውሮፓ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሁነው ከመጡት ከአቡነ እንጦስ ጋር በካድሪዎቻቸው አማካይነት ከለንደን ውጭ ያሉትን በደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የተቋቋሙትን ማህበር በቁጥጥራአቸው ስር አስገቡ። በኋላ የሸፊልድ ቅዱስ ሚካኤል በአል በሰኔ ሲከበር ሕዝበ ክርስቲያን ከተለያየ ቦታ መጥቶ ነበርና፣ ወደ ሀገራቸው ሊመለሱ በካድሪዎቻቸው አማካይነት ስጦታ ሊሰጡ ጥሩ መንፈሳዊ አባት እንደሆኑ ተገለጸ።

አቡነ ሙሴ ከሀገራቸው ወደዚህ የመጡት በሲኖደስ ለህክምና ተልከው ለአምስት ዓመት ሲታከሙ ቆይተው አሁን ህክምናቸውን ጨርሰው ወደ ሀገራቸው ሊመለሱ ነው ፤እኒህ ቅዱስ አባት በአምስት ዓመት ቆይታቸው ሐዋርያዊ አገልግሎታቸውን ሲፈጽሙ ቆይተዋል፣ እኛንም የአባትነታቸውን ምክር እየለገሱ አስተምረውናል፤ አሁን ይህ ስጦታ ለአባታችን በአቡነ እንጦስ እጅ ይሰጥልን አሉ። አቡነ እንጦስም እንባ እየተናነቃቸው የምወዳቸው አባቴ የማከብራቸው አባቴ ሊለዩኝ ነው በማለት በኀዘንና በእንባ ፍቅራቸውን ገለጹ። አቡነ ሙሴም የተላኩበትን ዓላማ አሟልተው ወደ ሀገር ተመለሱ።”የቀጣፊ እንባ ባቄላ ባቄላ ያህላል” እንደሚባለው እሳቸውም ቅጥፈታቸውን በህዝበ ክርስቲያኑ ፊት አሳዩ።

**““ዝከረ አበው”” መጽሔት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ተዘጋጀ። አዲስ አበባ (ትቅምት፡፲፱ ፺፮ (1996) ዓ/ም)**

***ማሳሰቢያ፤***

***በዚህ መጽሔት ውስጥ ከተመዘገበው የሚከተለው ይገኝበታል።***

**“ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ለከፍተኛ የሐዋርያነት ተግባር መርጣ ከሾመቻቸውና በሕይወት ካሉት መካከል በዚህ ዝክረ አበው መጽሔት ፎቶግራፋቸው ያልተቀመጠ፣ስማቸው ያልተመዘገበ ሊቃነ ጳጳሳት ወኤጲስ ቆጶሳት እንደ ነበሩ የታወቀ ነው፤ እነርሱም ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ለምን ተጣሰ ብለው ሀገራቸውን ጥለው፤ ቤተ ክርስቲያናቸውን ትተው ወደ ውጭ ሀገር የኮበለሉ ናቸው።**

**በዚህ ምክንያት**

**1ኛ. አባ መልከ ጼዴቅ**

**2ኛ. አባ ዜና ማርቆስ**

**3ኛ. አባ ይስሐቅ**

**4ኛ. አባ ኤልያስ**

**5ኛ. አባ ጎርጎሬዎስ**

**በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ወክለው እንዳይሰሩ፤ ጥር ፲ ፬ቀን ፲፱ ፻፹፯ (14/1987፤ዓ/ም) በተደረገው የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ተወስኗል። ይጠሩበት የነበረው ስመ ተጸውዖም አሁን በሥራ ላይ ላሉት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ወኤጲስ ቆጶሳት እንዲሰጥ ተደርጓል። ከዚህም ሌላ ብፁዕ አቡነ ገብርኤ ሊቀ ጳጳሳና ብፁዕ አቡነ ሙሴ ጳጳስ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ጥሰው ለግል ፍላጎታቸው ከሀገር ወጥተዋል። ሆኖም ቀደም ሲል በተፈጸመው ድርጊት ሁሉ ተጸጽተው ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸው ከተመለሱ ቤተ ክርስቲያናችን በሮቿን ክፍት በማድረግ ትጠብቃቸዋለች” ይላል።** እንግዲህ ተመልከቱት መነኩሴ ሲዋሽ ማለት ይህ ነው።በአባ ጳውሎስ ስም የተዘጋጀው መጽሔት ከሲኖዶስ ውጭ ሁነው ከሀገር ወጥተው መኮብለላቸውን አረጋግጦ የውግዘት ቃል አስተላልፎ ያስቀመጠውን። እነሱ ግን ሲኖዶስ ለህክምና እንደላካቸው አድርገው አቀረቡ። አንደኛ አቡነ ሙሴ መርቀው በከፈቱት በለንደን ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ስጦታው ተዘጋጅቶ ሲያበቃ በሚያውቃቸው ሕዝበ ክርስቲያን ፊት ያልተደረገበት የመነኩሴ ውሸታም ስለሚያሰኛቸው ምክንያት ተፈልጎ ሽፊልድ ሚካኤል አምጥተው ሰጡአቸው።

ነገር ግን ሕዝቡ ለአምስት ዓመት ያህል ኢሚግሬሽን ኦፊስ (Emigration Office) የመኖሪያ ፍቃድ ከልክሏቸው እንደ ነበረ ያውቃል። **“በመጨረሻም የመሰናበቻ ንግግር ሲያደርጉ ፖለቲካውን ትታችሁ በቤተ ክርስቲያን ተሰባሰቡ አገራችን እንደሆነች ከጥንት ጀምሮ ነው ማላትም እኛ ከተወልድን ጀምሮ እንዲሁናት የተለየ አይደለም ብለው ተናገሩ።”** ታዲያ አሁን ይህ ከአንድ የክርስትና እምነት ተከታይ ከሆነና ታስሮ ከተገነዘ መነኩሴ የሚወጣ ቃል ነው።

ከመቼ ወዲህ ነው ኢትዮጵያ እንዲህ አይነት መከራና ችግር ደርሶባትና አጋጥሟት የሚያውቅ?። ዙሪያ ጥምጥም ሄዱ እንጂ ዝምብላችሁ ለወያኔ ተገዙ በዬ አደባባዩ እየወጣችሁ ጭሆት አታሰሙ፤አታብዙ አትረብሹ ወያኔን ጠልታችሁ ለጠይ አትስጡት ማለታቸው ነው። ሀገር ቤት ያለው ሲኖዶስ በህጋዊ መንገድ ለሰሜን አውሮፓ ሀገረ ስብከት ሹሞ የሰደዳቸው ጳጳስ በካድሪዎቻቸው አመካይነት ገንዘብ ለመዝረፍ ተፈልጎ  በምን ምክንያት እንደመጡ ሕዝቡ የማያውቅ አስመስለው አባታችን አቡነ እንጦስ ተቸግረው የቤት ክራይ የሚሆናቸው መቶ ፓውንድ በየወሩ ተቆራጭ ሊያደርጉ ለማህበሩ ጥያቄ ሲያቀርቡ? ማህበሩ አልስማማ ሲል በድምጽ ብልጫ እናደርገዋለን ብለው ለሳምንት ቀጠሮ ተያዘ። በሳምንቱ ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ ለሆነው ሁሉ የመድኃኔ ዓለምን ንብረት ሊዘርፉት ነው ድረሱልን ተብሎ በስልክና እንዲሁም በቴክስት ተነገረን። የሌባው ቡድን የማስፈራሪያ ቃላት እየተጠቀሙ በከፊል ማህበሩን አሳምነው ተዘጋጅተው መጡ። ለብዙ ጊዜ ከማህበሩ እርቄ ስለነበር የዚያን እለት በቦታው ስገኝ ደስ አላላቸውም ነበር። ጸሎት እንደተደረገ ትምህርተ ወንጌልን ሳያስተምሩ በቀጥታ ወደ ጉዳያቸው ገቡ። አባታችን የሚበሉትና የቤት ክራይ የሚከፍሉት ገንዘብ የላቸውም እንደመጡ በፊት የጀማይካ ቤተክርስቲያን ነበርች ችላቸው የነበረ፣ አሁን ግን እነሱ ቦታውን ስለ ለቀቁ የሚረዳቸው የለም ስለዚህ ማህበሩ መቶ ፓውንድ በየ ወሩ ከቤተክርስቲያኗ ገንዘብ እንድንከፍል

ወስኗል ብለው በጽሑፍ መልክ አቀረቡ። ዓይን አውጣው የሌባ ደረቅ ማህበሩ ስላልተስማማበት ሁሉም በፍርሃት ተውጦ የሚናገር ጠፋ የሚደግፍም የሚቃዎምም የለም ሁሉን በዓይናቸው እየገላመጡ ያዩታል፤ ጸጥታው እንደሰፈነ ቆየ። በኋላ እኔ እጄን አውጥቼ ጥያቄ አለኝ አልኩ፥ "ገልመጥ አድርጎ አንተን አይመለከትህም ሲል" ለምን አይመለከተኝም ብዬ በደም ፍላት አላስፈላጊ የሆነ ቃላት ወረወርኩ። ባላጋራየም ያልጠበቀው ነገር ሲደርስበት እንደቆመ ከዚያው ኩምሽሽ አለ። ማህበሩን ካቋቋም ነው አንዱ እኔ ስለነበርኩ እንዴት አያገባህም ትለኛለህ ብዬ ንትርክ ውስጥ ገባሁ። ሕዝቡም በሁለት ጎራ ተከፈለ በጉዳዩ አብረው የተስማሙት ሳይቀር በነገሩ ስገፋበት ተው ይናገር ይናገር ብለው እድል ተሰጠኝ። አንደኛው ጥያቄዬ ሕዝበ ክርስቲያኑ ለምን ተበተነ ሁለተኛው ጳጳሱ ወደ ዚህ አገር እንዴት መጡ? ጥገኝነት ጥይቀው ነው ወይስ በመንግሥት ተልከው ነው ስል፤ በሁለቱም በኩል መልስ የለም። ቤተ ክርስቲያኗም ሲኖዶሱም በወያኔ ቁጥጥር ስር ስለሆኑ ወያኔ እንጂ ሲኖዶሱ አቅም እንደ ሌለው ስለማውቅ በመንግሥት ተልከው ነው ወይ ያልኩት ለዚህ ነው። በኋላ ከታለሉትና ከተገዙት ስለቤተ ክርስቲያን የማያውቁ እንዲሁ በደፈናው ከአባታችን በረከት እናገኛለን ይከፈል ይከፈል አሉ። የእግዚአብሔርን ገንዘብ ለዲያብሎስ ሰጥተው በረከት ሊያገኙ ተንጫጩ አይፈረድባቸውም በደካማ ጎናቸው ስለገቡባቸው ነው። እኔም ስለ አባትነታቸውና ስለ አመጣጣቸው እንዲነግረኝ ብዬ ካድሪውን አፋጥጬ ያዝኩት። ወገኖቻችን በወያኔ ጥይት ሲደበደቡ አንድ ቀን ወጥተው ስርአቱን ያላወገዙ ውግዘቱም ይቅር ለሞቱት ሰዎች ቤተሰብ እንኳ አላጽናኑም።

በእግዚአብሔር ቁጣ በውሃ ላለቁት ለእሲያ አገር ሰዎች በአዋጅ አስነግረው ፍትሐት ሲያደርጉ ለገዛ ሕዝባቸው ግን የማጽናኛ መእልክታቸውን እኳ አላስተላለፉም። አባ እንጦስን ብቻም ሳይሆን አባ ጳውሎስን ጭምር ነበር፣ ከጥያቄየ ውስጥ ያስገባኋቸው። ቀጥየም በጎንደር በአዲስ አበባ በጅማና በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የደረሰውን ጭፍጨፋ አንስቼ ይህ ሁሉ ሲፈጸም አብረው ከወያኔ ጋር አድመው ሕዝባቸውን ያስፈጁ አሁን አባታችን ብላችሁ በደና ጊዜ እኛ ያሰባሰብናትን ገንዘብ ልሰጡ ተስማማችሁ፣ይህማ አይሆንም ብዬ ተናገርኩ። "ሥለስራቸውም በእንተርኔት ሁሉም ሰው የሚያውቀው ስለ ሆነ የሰው ኃጢአት ማቅለል ነው" አለኝ። ከዚህ ያለ ሰው እንኳን ስለቤተ ክርስቲያን ይቅርና ስለራሱ ወደ ዚህ አገር ለምን መጣህ ተብሎ ቢጠየቅ መልስ መስጠት የማይችል መለሶም ስለሀገሩ የማያውቅ ሁሉ ያውቃል ትለኛለህ ብዬ ነገሩን ስቀጥል። እንደማይሆን ሲያውቁት ገንዘቡ አይሰጥም በቃ በዚሁ ይቁም አሉ። ከሳምንት በኋላ ጳጳስ ተብየው ከበረከት ስምዖን ከሌሎች ባለስልጣን ጋር በኤምባሲው በራፍ ቁመው በጋዜጠኛ እንተርቪው(ቃለ መጠየቅ) ተደረገላቸው። ለጋዜጠኛ የሰጡት መልስም ሳያፍሩ ደበኛ የወያኔ ካድሪ ሞሆናቸውን አጠንክረው ተናገሩ። ቅዳሴ ቀድሰው ሲጨርሱ አንድ ቀን እኳ ተሳስተው ለሀገራችን ሰላም ለሕዝባችን ፍቅርና አንድነትን ስጥልን ብለው እግዚአብሔርን ለምነው በጸሎት አያሳርጉም። የመባእ ገንዘብ አንሶ ከታየ እንደገና አዋጡ ብለው ሙዳየ ምጽዋት ያዞራሉ በገንዘብ ፍቅር የተነኩ ናቸው። ብዙዎቹ ለምን ዝማላችሁ ተብለው ሲጠየቁ አገር ቤት ስንሄድ ጠቁመው ያሲዙናል መልሶም ቤት ሰቦቻችን ያሳቃዮአቸዋል ለዚህ ነው እያወቅን ዝም ያልነው አሉ። መቼም የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉራማይሌ ነው በእምነቱ የጸና አይደለም። የእግዚአብሔርን ትቶ የሰውን ነው የሚያየው ሥጋውን እንጂ ነፍሱን አልወደደም ጥቅምን እንጂ እምነትን አልፈለገም።

ሌሎችም እንዲሁ መነኩሴና አንዳንድ ወንጌል ሰባኪያን አማራ ሳይሆኑ አማራ ነን የሚሉ አሉ ሀገር ቤት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ወይም ስርአት ተቃውመው መጥተው ከዚህ እጅ ይሰጣሉ። ወረቀታቸውን ከአገኙ በኋላ ተመልሰው ከዚያው ቡድን ይቀላቀላሉ። እንዲያውም ሰዎችን አታሎ ለማስገባት ሲባል ያልተወለዱበትን አገር አገሬ ብለው የትውልድ ቦታዬ ከዚያ ነው የሚሉም አልጠፉ።አንድ ነገር አስታወሰኝ በደርግ ዘመን ከወሊጋ ጎንደር ወገራ አውራጃ ዳባት ከተማ ብሄራዊ ውትድርና ሊሰለጥን ይመጣል፤ የነበረበትን ካምፕና የአካባቢውን ስም ያውቀው ነበር። ከእለታት አንድ ቀን በጦር ሜዳ ላይ በሻዕብያ ወይም በወያኔ ተማርኮ ወይም ከነበረበት ጦር ከድቶ ይሆን አላውቅም፣ ሱዳን ሀገር ሀምራ ኩባ ከስደተኛ ካምፕ ይመጣል። በወቅቱ የስደተኛው አላፊ የነበሩት የጎንደርና የጎጃም ለዚያውም የዳባትና የቁንዝላ ተወላጆች በሆኑ ሰዎች ነው ቦታው ተይዞአል እየተባለ ሲነገር ሲሰማ፤ ያ ከወሊጋ የመጣ ሰው የዳባት ተወላጅ ነኝ ስል፤ እንደ ወንድም አይቶ እርዳታ ይለግስልኛል ብሎ አሰበ። አማርኛውን ሳያጣራ ቀረበና ለአላፊው "የዳባት ሰው ነኝ" አለ። አላፊው "ዳባት የት ላይ" ብሎ ሲጠይቀው ያችን የሰለጠነባትን ቦታ አላጠፋትምና "ጥቁር ባሕር" አለ። አላፊውም ስሙን መጥራት

አልፈልግምና “አፍህ እየመሰከረብህ ዳባት ነኝ ትለኛልህ ደግሞስ ኅጠኛ ነው ያልህ ማነው” ብሎ አንዴ በጥፊ ሲያጮለው። “ኧረ ጌታዬ ሰዎች ናቸው የዳባት ልጅ ነኝ ካልከው ይረዳሃል ብለውኝ ነው፤ እንጂ እኔ አይደለሁም” አለ። ጥፊውን ከቀመሰ በኋላ እውነት ስለተናገረ ለአምስት ሰው በቡድን የሚሰጠውን እቃ በሙሉ ለብቻው ተቀበለ። ከዚያ በኋላ ጥፊዬ ጠቀመችኝ እንጂ አልጎዳችኝም እያለ ያስቀን ነበር። እኛም ቅጥል ስሙን ዳባቴው እያልን እንጠራው ነበር። ሰውየውንም ወደደው እንጂ አልጠላውም ምክንያቱም ውሸት ጎጅ እንጂ ጠቃሚ እንዳልሆነ መልሶም ያልሆነውን ነኝ ማለቱ አሳፋሪ መሆኑን ስለተረዳ። እነዚህ ደግሞ  ሰላም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ ሊሉ (ሰላም ለቺ እንዘ ንሰግድ ንብለቺ) እያሉ አማራ አለመሆናቸውን ምላሳቸው እየመሰከረባቸው አጥብቀው ሲጠየቁውና ሲመረመሩ ግን አይ ተወልጀበት አለሁ እንጂ አላደኩበትም ይላሉ። እኒህንም የመነኩሴ ውሸታም ብለው እንደ ወታደሩ አንዴ በጥፊ ቢያጥወለውሏቸው በል ተብየ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም ማለታቸው አያጠራጥርም ነበር። ወታደሩስ የሰለጠነበትን ቦታ ተናገረ መነኩሴው ግን ዳባት የሚለውን ስም ብቻ አወቁ እንጂ ሌላ ሊጨምሩ አልቻሉም። አንዳዶቹም የአካባቢው ተወላጅ የሆኑ ሰዎች የነ ማን ወገን ናችሁ ሲሏቸው የነ እከሌ ወገነን ማለት ሲያቅታቸውና መልስ ሲያጡ አይ ተምሬ በታለሁ እንጂ አልተውለድኩበትም ይላሉ። ታዲያ ካህናቱ ሳይቀር ያልሆኑትን ሁነናል ማለት የእነሱ የጎጠኞች ሥራ ከሆነ ውሎ አድሮአል። መልሶም እንዲህ እየሆኑ ይጋለጣሉ። እኛ የምናውቀው የሃይማኖት ትምህርት የቀሰመና መነኩሴ የሆነ ሰው በአንዲት አገር እንጂ በተወለደበት ሰፈርና መደር አያምንም። የነዚህ ግን የተለየ ነው። ልክ እንደ ፖለቲከኞቹ ሃይማኖተኛ ነን የሚሉትም የዘመዶቻቸው በሽታ(ቫይረስ) ስለተላለፈባቸው እነሱም በጎጥና በብሄር ያምናሉ። አንድን መነኩሴ ለቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ አድርጎ ሲኖዶሱ ወደ ውጭ ሊልካቸው ከአባ ጳውሎስ ፊት ይቀርባሉ። የአባ ጳውሎስ የመጀመሪያው ጥያቄ ለመነኩሴው “አገርህ የትነው የሚል” ነበር። መነኩሴውም ሲመልሱ “አገሬ ኢትዮጵያ እንጂ ሌላ ሀገር የለኝም “ይላሉ። አባ ጳውሎስም “ኢትዮጵያ ማ ሁላችንም ኢትዮጵያዊ ነን፤ ግን ሰዎች ስም ይሰጡናል” መነኩሴውም “ታዲያ ሌላ ምን ሀገር አለ” አባ ጳውሎስ ግን የትውልድ መደራቸውን እንዲነግሯቸው ፈልገው ነበር። መነኩሴው፤ ግን “እኔ ሀገሬ ኢትዮጵያ እንጂ ሌላ ሀገር የለኝም” ብለው ሲዘጉ። አባ ጳውሎስም የመነኩሴው መልስ ስላ ላስደሰታቸው ለሰባት ወር ያለምንም ክፍያ አዲስ አበባ አስቀምጠው ካጉላሏቸው በኋላ ለአባ ጳውሎስ ታማኝና ወዳጅ በሆኑ ጳጳስ በአስር ጣታቸው ተፈርሞላቸው እንደዘመዶችህ እንዳትከዳ ተብለው አባ ጳውሎስ የራሳቸውን ካድሪ በበላያቸው ሸመው ሰደዷቸው። እስከዚህ ድረስ ነው ቤተ ክርስቲያን በወያኔ ዘረኞችና በጎጠኞች እየታመሰች ያለችው። ከእምነት ይልቅ ፖለቲካ ውስጥ የሚገቡ፣ ከእውነት ይልቅ ክህደት የሚያበዙ፣ ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ከግለሰብ ቤት እየሄዱ ሲያጎበድዱ የሚውሉ፣ ከጸሎት ይልቅ ኃብት የሚያከማቹ፣ ከነፍሳቸው ይልቅ ሥጋቸውን የሚወዱ፣ ከመስጠት ይልቅ መቀበልን የሚፈልጉ፣ ከመጾም ይልቅ መብላትን የሚያዘወትሩ። ታዲያ እኒህ ሃይማኖት ያላቸው መነኮሳት ናቸው ወይ? ወይስ አሕዛብ። እነሱ በጥላቻና በተንኮል ተውጠው በብረት ሰንሰለት እጅ እግራቸውን ታስረው እራሳቸው ሳይፈቱ መስቀል ጨብጠው ሰውን ሲያሳልሙና የሞተ ሰው እንፈታለን ሲሉ አያፍሩም። **አሁንም በሀገር ቤት ያላችሁትም በውጭ አገር የምትኖሩት ካህናት የምትሰሩትን ሥራ እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ ሁሉ አውቆባችኋል ከዚህ ከያዛችሁ ከሰይጣን ቁራኛ ተሎ ብላችሁ ንስሐ ገብታችሁ ተላቀቁ። ካለበለዚያ ግን የእግዚአብሔር ክንድ በእናተና ግፍ በፈጸሙት ባለስልጣናት ላይ እንደተዘረጋ ነው።አልፈው ከሄዱት ትምህርት ውሰዱ እናንተ ሰውን ንስሐ ግቡ ትላላችሁ ከማን አይቶነው ንስሐ የሚገባ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እሱ መከራን ተቀብሎነው የጽድቅን፤የፍቅርንና የንስሐን መንገድ ያሳየ። እናንተም ተስማምታችሁ ለአንዲት ቤተ ክርስቲያንና ለአንዲት ሀገር ስትሉ መከራን ተቀብላችሁ የጽድቅን፤የንስሐንና የፍቅርን መንገድ እያሳያችሁ ስትሰብኩ ሕዝበ ክርስቲያኑ ይቀበላል መልሶም እናንተን አምኖ ይከተላችኋል።**

ትንቢቱ ደረሰ አረጀ ዘመኑ
ወንዶችም ሴቶችም አንድነት ተካኑ።

መጨረሻው ዘመን ደረሰና ቃሉ፤
በካህናት ወንበር ሴቶች ቁጭ አሉ፤
የቤተ ክርስቲያን ስርአት ፍጹም ጠፋ ውሉ፤
ቆብ የሜኑት ሁላ መነኩሴ ነን አሉ፤
ከወታደር ጋራ አብረው እየዋሉ፤
እኛ ካህናት ነን አዳምጡን ይላሉ።

አቡነ፤ ሚካኤል፤ አቡነ፤ ጴጥሮስ፤
አሁን ባያችሁልን በቅዱስ በመንፈስ፤
ቤተ ክርስቲያናችሁ እንደዚህ ስትፈርስ፤
ከሃዲዎች በዙ ቀሳጢም ጳጳስ።

እባክህ ፈጣሪ አትጨክንባት!
ለቤተ ክርስቲያን ቅን አገልጋይ ስጣት፤
ተምሮ የሚያስተምር የጸና በእምነት፤
ሥጋውን በድሎ ነፍሱን የሚያድናት።

እውነተኛ መሪ አንተው ፍጠርላት፤
በአንተ የሚመካ ጥነት እንደነበራት፤
ዘብ ሁኖ የሚቆም ለሀገር ለሃይማኖት።

ተማለደን ጌታ ቸሩ መድኃኔ ዓለም፤
ይቅር በለንና ፍቅር ስጠን ሰላም፤
ርስ በርሳችን እየተወጋገዝን አንኑር ዘላዓለም።

<u>እግዚአብሔር ሀገራችንና ቤተክርስቲያናችን ይጠብቅልን አሜን!!!</u>

<u>ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!!</u>